"<u>የሶምሶን ኑዛዜ</u>"

(ዓይኑ ታውሮ በጨርቅ የተሸፈነ በሰንሰለት ያታሠረ ወጣት ይታያል)

ኡፍ...

ሃሳብም እንደሥጋ ምናለ ቢጨበጥ ቢታሠር

አካል ግዘፍ ወስዶ ነስቶ እንዲህ በብረት ቢታሠር

እግሩ እንዳይል ወዲህ ወዲያ አንድ ቦታ ቢቸነከር

ኡፍ...

ምናለ የሰው ልጅ ባያጠፋ ምናለ ከበደል ቢፀዳ

ወይ ካጠፋ በኋላ ጥፋቱን ሁሉ እንዳይረዳ

መልሶ መክፈል ላይቻለው የህሊናውን ውዝፍ ዕዳ

በፀፀት ልቡ ተሸንቁጦ ቁጭት መንፈሱን እንዳይመትረው

የትናንቱን እያነሳ ውስጡን ሰላም የሚነሳው

ህሊና የሚሉት ነገር ባይኖር

እኽ...

ሶምሶን ... ሶምሶን ተላላ...ሶምሶን ታላላ

አግዜር ይይልሽ አንቺም ደሊላ

እሷ ነች ይህን ያረገች ዋነኛ ምክንያት የውድቀቴ

እሷ ነች የገደለቺኝ ደሊላ ነች ጠላቴ

ሳልታወር ያወረቺኝ በመውደዷ ምትህት ሥራይ

አዚሟን ያዞረቺብኝ ዐይኔ ፈጦም እንዳያይ

በውበቷ ያሰረችኝ ያደረገችኝ የፍቅሯ ባሪያ

በትንፋሿ ወላፈን አንድዳ ያረመጠችኝ ቋያ

እሷ ነች እንቁዬን የጣልኩላት እርያ

አልቅሳ ተነፋርቃ የወደደችኝ መስላ

በውበቷ በሙቀቷ ልቤን አቅልጣ አባብላ

ዳብሳ ደባብሳ አሟሙቃ ውስጤን አማ ደልላ

ጉድ ሰራችኝ ደሊላ

አግዜር ይይልሽ ደሊላ

ዳሩ አንቺ የት ስታቂው እንዲህ ለጉድ ያስዋበሽን

እሱን ብታቂ ኖሮ ባልበደልሽበት ውበትሽን

በክህደት ምላጭ ባልላጨው የፀጋው ማደሪያ ፀጉሬን

ግና አልፈርድም ከዱ ባንቺ እኔ ሶምሶን ነኝ የማልረባ

እንኳንስ አንቺና ስሙ ከጆሮሽ ያልገባ

ከእናቱ ጡት ወተት ጋር ያደኩኝ ስሙን ስጠባ

ሀይሉን ያደለኝ ናዝራዊ ፀጉሬን በፀጋው የቀባ

እኔ ራሴ መች አወቅኩት ልቤ በእምነቱ መች ተባ

እኔ ሶምሶን....

አያርገውና የዛሬ

የፀጉሬ ጉልበት ሰርጎ ገብቶ ተዋህዶ ከጇ ከግሬ

እልፉን በግራ እልፉን በቀኝ አዝመራ እንደደራ ገበሬ

አንገት አንገታቸውን አጭጇ ቀንጥሼ ሰብስቤ ከምሬ
አበራያቸው ነበር እንደበሬ
እኔ ሶምሶን....
እንዲህ ሊያስረኝ አንድ አለንጋ
አንዴ ብቻዬን ጨረስኳቸው ሁሉን ባህያ መንጋጋ
ከነጦር ከነጋሻቸው ሳልሔድ ጋሻ ጦር ፍለጋ
ሶምሶን መጣ ሲባል ገና ድምፄ ከሩቅ ሲጠጋ
ውሃ ይሆን ነበር ሀሞታቸው ባጥንት ውስጥ ነበር መቅኔ ሚረጋ
እኔ ሶምሶን...
ዘሎ ሊያደቀኝ በክርኑ
እሱ አንበሳ በመሆኑ
ቢከመርብኝ አንበሳ ስለእኔ ዝና ያልሰማ
ከሁለት ቦታ ሰነጠኩት እጁን ይዤ እንዳከርማ
እኔ ሶምሶን...
ታዲያ እንዲህ ያደረገኝን አምላ አጥንት አፅንቶ ያበጀውን የኔን ሥጋ
እኔ ራሴ መች አወቅኩት የፀጋዬን አልፋ ኦሜጋ
የለም...የለም
ሰው አልኮንንም ሰው አላማም
እናው ነኝ የኔው ጠላት ወድጇ ባልረታላት
እኔን ሶምሶምን የሚረታ ደሊላ ምን ጉልበት አላት
ማ ጉልበት ሰጣት
ወድጇ ባልቀባቸር የልቤን ምስጢር ባላወጣ
ማ ፀጉሬን በላጨ ማን አይኖቼን ባወጣ
የትኛው የሞት ልጅ ነው ደፍሮ እጇን ሊይዝ የሚመጣ
የምላስ ጉድ ነው ይሄ ጣጣ
አፈ ነው የኔ ጠላት እሱ ነው የኔ ባላንጣ
እግዜር ይይልህ አፈ እግዜር ይይልህ አፈ
የአምላንና የወዳጇቼን ማስጠንቀቂያ ተላልፈ
ባተ ነው የተሸለትኩት በል ሳይለኝ ለፍልፈ
ፀጋዬም አብሮ ከፀጉሬ የተገፈፈው ከራሴ
ባንተ ጦስ ነው ምላሴ
ያ ምስኪን ዮሴፍ ህልመኛው
በወንድሞቹ የተሸጠው
ህልሙን አውርቶ ነው አሉ ሲበዛ ህልመኛ በመሆኑ
የግዛ ወንድሞቹ የሸጡት እውን ባሆነ ህልሙ ስለቀኑ
የሱስ ህይወት አዳነ የህልሙ ወሬ ኃላ ዘግይቶም እንኳ ቢሆን
ይብላኝ ለኔ ለመከረኛው ህልሜን ላወራሁ በሰመመን
ወይኔ ሶምሶን....
ምን ያደርጋል አሁን ምላስ የሚሉት ትርፍ ስጋ
ሰውን የሚያክል ግዙፍ አካል አጋልጦ ከሚሰጥ ላደጋ
ምና ቢነቀል ቢመነገል አልያም ቢጠጋ ከትናጋ

ያልበደለውን ምስኪን አይኔን በጋለ ብት ከሚጓጥጡት

ምላል ምላሴን ቢቆርጡት ምናል አፈን ቢለጉሙት

የነፍስን ትልቅ ምስጢር አፍ ቀዳዳ ሆኖ ከሚያፈስ

እና እሱስ ቢዘጋ አፍንጫ አይበቃም ለመተንፈስ

ለካስ..ለካስ... በእሱ ነው የሚጠጣው ለካስ በእሱ ነው የሚጎረስ

ረሳሁት እኮ ቀናት ቢያልፉኝ እንዳች ሳልበላ እህል ሳልቀምስ

ጥርኝ ውሀንኳ ካፈ ሳይደርስ

እህል ለአፍ ብቻ ቢሆን ውሀም ለምላስ ማረስረሻ

ያለበደሉ ለጠፉ አይኔም እንዲሆንልኝ መካሻ

አፈ ምላሴ እንዲደርቁ እንደበጋ ምድር እንደበጋ እርሻ

የእስራኤል አምላ ምስክሬ ነው እህል ውሀም አልሻ

ብቻ ብሻስ ማን ይሰጣል

አፍ ሁሉን አስነጥቋል

ኡፍ

ምና የሰው ልጅ ባያጠፉ ምናል ከበደል ቢፀዳ

ወይ ካጠፉ በኋላ ጥፋቱን ሁሉ እንዳይረዳ

መልሶ መክፈል ላይቻለው የህሊናን ውዝፍ እዳ

ፀፀት ልቡ ተሸንቁጦ ቁጭት መንፈሱን እንዳይመትረው

የትናንቱን እያነሳ ውስጡን ሰላም የሚነሳው

ህሊና የሚሉት ነገር ባልኖረው

ኡፍ...

ለነገሩ ሳስበው ልቤ አስቀድሞ ባይወዳት

አፈ ምስጢሩን ባላወጋት

እኮ..እኮ..ልቤ ነው ጠላቴ አፈ ምንም አልበደለ

በልብ ያልተዘራን ክፋት አፍ ከወዴት አበቀለ

አፈ መች ይናገር ነበር ልቤ እሺ ብሎ ባላቀበለ

እግዜር ይይልህ የኔ ልብ ልቤ እግዜር ይይልህ

አይኖቹ እንደጠፉ ያጥፋህ

እንዳዋረድከኝ ያዋርድህ

ምስጢር ቁምነገር በሞላ ልብ ውስጥ ነው መቀመጫው

ልቤ በአፉ ለአፈ የልቡን ምስጢርማን ንገር አለው

ፊዕሞ በአፈ አይደለም የልብ ምስጢር የሚዘራ

ፊት የልብ አፍ ሲከፈት ነው በውስጥ ለራሱ ሲያወራ

ልብ ሲያመነታ የተፋውን አፍ ይሰማዋል በውስጥ ጆሮ

ይሔኔ የውጭው አፍ ወደ ውጭ ይተፋዋል አንቅሮ

አዎ ልክ ነኝ...ልቤ ነው ጠላቴ ከኔ ደሊላን የወደደ

ኃላም ከውስጤ ላይወጣ የግሏ ሊሆን የሔደ

የልቤን ምስጢር እንደያዘ እኔን የሸጠ የካደ

ባንዳ ለጠላት ያረገደ

በእጇ ስትነካው የተቀደደ

ጥብቅ ምስጢሩን የሰደደ

ልቤ ነው እኔን ያዋረደ

ኡፍ...

አሁን ማሰብ ማገናዘብ

መላ አካልን መሰብሰብ

የሰውን ሀላፊነት በሙሉ

መመርመር ማስተዋሉ

ይቺን ጭብጥ ለሚያክለው

ለልብ መስጠት ተገቢ ነው

ትንሽ ትልቅ ጠቢብ ዝንጉ

መፅዋች ሌባ ለጋስ ንፉጉ

የዋህ ጨካኝ ክፉ ደጉ

የሰው ልኩ የሰው ጥጉ

ማረጉ

የውስጥ ቀለም ነጠብጣቡ

የነፍስ ከስጋ ስምረት አሰካኩ አገባቡ

የሰው አይነት የነፍስ ቅቡ

እንዴት ይለካል በልቡ

ኤድያ.....

ሀሳብም እንደስጋ ምናል ቢጨበጥ ቢታሰር

አካል ግዘፍ ወስዶ ነስቶ እንዲህ በብረት ቢሰተር

እግሩ እንዳይል ወዲህ ወዲያ አንድ ቦታ ቢቸነከር

ኡፍ...

ለነገሩኮ አይኔ ባያያት ጆሮዬ ድምጿን ባይሰማ

ልቤ ያ ብርቱ ልቡን ባልተቀማ

የለም የለም አይኔ ምን ይሁን

በደንብ ግራ ቀኝ ካላየ እንዴት ይሔዳል መንገዱን

የልብ ዐይን ካላየ የስጋ አይን መች ያይና

በዐይኗ ዐይኑን የቃኘ ልቤ የዐይኔ ብርሃን ያላት ላምባዲና

በፈልስጤሞች የሚሞላ መርዛም ሳምባዋን ሳያጠና

ለነገሩማ

ልቤ አንዴ እንዳያት - በፍቅሩ ሞራ ተጋርዶ

ረዳት ዐይን እንደሚፈልግ የሚያይለት ሞራውን ቀዶ

ክፉና ደጉን የሚለይለት ዐይኖቹን አርቆ ሰዶ

መላ አካሌም ረድቷል ምን ቢሆን ትንሽ አርፍዶ።

እና ይህንን እያየ ዐይኔ እሱም ሲያያት መራቡ

ቀንደኛ ተጠያቂ ነው በመመለሱ በውር ልቡ።

እግሬ በመሄድ ካለችበት እጇ ገላዋን በመዳሰስ

ባዞ እንባ ሊቀጥን ሊሟሟ ክንዴ ራሷን በመንተራስ

በአልንጋ ጣቷ ሊቆፈር የምሥጢር ቦታ የኔም ራስ

ከጭን ጉልበቷ በመጎነበስ

ጆሮዬም ካፏ ተሻርኮ ያን ቅላጼዋን በማስገባት

ሁለመናዬን ተቆጣጥራ ስታጋድመኝ በልዩ ምትሀት

ልቤ ሌላውን አንዳይሰማ ሸፍኖ ደፍኖ አደንቁሮ

ይኸው አስጠቁና አካላቱ የወደደችውን አመቻቹላት

ኡፍ...

እኔነቱ ሰውነቱ መላ አካሌ በጠቅላላ

ተገዝቷል ለደሊላ

የጠላቱ ወዳጀጅ ደሞ ጠላቱ ነው ይህ እምነቱ ነው የሁሌ

ሺ ጊዜም ቢሆን የገዛ አካሌ

እናም ሰሙኝ አካላቱ

ወዳጅ ሆናችሁ የጠላቱ

እንዳጣላችሁኝ ከወዳጄ

እርቃኔን እንዳስቀራችሁኝ ልዩ ፀጋዬን አስወስጄ

አበቀላችኋለሁኝ በእጄ

በደህና ጊዜ ተገላግለሀል-ዐይኔስ ክፉውን እንዳታይ

ጆሮዬ ግን ትሰማለህ - ገና ሲያላግጡብኝ በአደባባይ

ሞት ሞት ለሁሉ የማይቀር አንድ ነው

የጀግና ሞት ግን የሚለየው

ማርከሻ እንዲሆን ለቁጭቱ

ሥራ ይሠራል ሞቱ (ተንበርክኮ)

ከናቴ ማህፀን የመረጥከኝ

ፀጋህን በገፍ ያደልከኝ

ከዛ ከፀጋህ ቆንጥረህ ላዛሬ ብቻ ትንሽ ስጠኝ

ጠላት አንዳይመካ በጉልበቱ

መልሰህ አድርገኝ ብርቱ

እንዳትታመ በእኔ ድካም

በፊታቸው በብርታት ልቁም

አምላክህ የታለ ብለው በስምህ እንዳይዘብቱ

መልሰህ አድርገኝ ብርቱ

ላፍርሰው አደባባዩን ሰገነት መድረኩን በጠቅላላ

ክፉዎች ይደምሰሱ አብራ ትጨፍለቅ ደሊላ

ሥጋዬም አብሯቸው ይሙት አልፈልገውም ከዚህ በኋላ

መቼስ ከየም ይመጣል በግና ጊደር

ከየት ይገኛል አሁን ካህን

ቀኖና ይሁነኝ ቅጣቱ

ኦዛዜም ንስሐ ይሁን አሜን ለይኩን።

(ወታደር ይመጣል)

ወታ፡- ፈጠን በል ተከተለኝ

ሶም፡- ዋና ምሰሦው ላይ እሠረኝ…

(የመፍረስ እና የኳኳታ ድምፅ ይሰማል)